# ቤተ-መጻህፍትንና ልማትን አስመልክቶ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን ያወጣው መሪ-ሃሳብ

መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት የድህነትን አዙሪት የሚሰብር እና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት የሚረዳ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብት ነው፡፡ በብዙ ማህበረሰቦች ዘንድ ሰዎች ትምህርታቸውን ለማሻሻል፣ አዳዲስ ችሎታዎችን ለማዳበር ወይም ሥራዎችን ለማግኘት፣ የንግድ ሥራዎቻቸውን ለማሳደግ፣ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የግብርና ወይም የጤና ውሳኔዎችን ለመወሰን፣ ወይም ስላለው የአየር ንብረት ሁኔታ በቂ ግንዛቤ ለማግኘት እንዲረዷቸው መረጃዎችን ለማግኘት የሚሄዱባቸው ብቸኛ ሥፍራዎች ቤተ-መጻህፍት ናቸው፡፡ መረጃዎች በተለያየ ቅርጽ በቀላሉ እንዲገኙ በማድረግና በዚህ በየጊዜው እየተለዋወጠና ውስብስብ እየሆነ በመጣ ማህበረሰብ ውስጥ ለመረጃ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አገልግሎቶችንና ፕሮግራሞችን በማቅረብ በኩል ያላቸው ልዩ ሚና ቤተ-መጻህፍትን እጅግ አስፈላጊ የልማት አጋሮች ያደርጋቸዋል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እ.ኤ.አ. ከ 2015 በኋላ የሚኖረውን የዓለም የዕድገት አቅጣጫ መሪ-ሃሳብ ለማበጀት እየተንቀሳቀሰ ባለበት በአሁኑ ወቅት በሁሉም የዓለም ክፍል ቤተመጻህፍት የዘላቂ ልማት እቅዶችን ለማውጣት አስተማማኝ መሣሪያዎች መሆናቸውን ሁሉም ባለድርሻ አካላት እውቅና እንዲሰጡት የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን ጥሪውን ያቀርባል፡፡ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን የሚከተለውን በአጽንዖት ይገልጻል፦

## ቤተ-መጻህፍት ለሁሉም እኩል ዕድል ይፈጥራሉ

ቤተ-መጻህፍት በሁሉም ሥፍራዎች ማለትም በገጠርም ሆነ በከተማ እንዲሁም በካምፓሶች እና በሥራ ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ ቤተ-መጻህፍት ዘርን፣ ብሄርን፣ ኀሣን፣ ጾታን፣ ዕድሜን፣ የአካል ወይም የአዕምሮ ሁኔታን፣ ሃይማኖትን፣ የኢኮኖሚ አቅም ደረጃን ወይም የፖለቲካ አመለካከትን ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ ሁሉንም ያገለግላሉ፡፡ ቤተ-መጻህፍት ለጥቃት የተጋለጡና የተገለሉ የማህበረሰቡን ክፍሎች የሚደግፉ ሲሆን ማንም ሰው መሠረታዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎቹ ወይም ሰብዓዊ መብቶቹ እንዳይነፈጉ በማረጋገጥ ረገድ ይረዳሉ፡፡

## ቤተ-መጻህፍት ሰዎች ራሳቸውን ለማሻሻል እንዲችሉ አቅም ይፈጥርላቸዋል

ቤተ-መጻህፍት በየትኛውም የማህበረ-ሰብ ክፍል የሚገኙ ሰዎች የሚማሩበት፣ የፈጠራ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበትና እና አዳዲስ ግኝቶችን የሚያገኙበት ህብረተሰብ እንዲፈጠር ይደግፋሉ፡፡ ቤተ-መጻህፍት የመማር ባህል እንዲሁም ሂሳዊ አስተሳሰብና መርምሮ የማወቅ ፍላጎት እንዲዳብር ይደግፋሉ፡፡ በቤተ-መጻህፍት አማካይነት ሰዎች የቴክኖሎጂንና የኢንተርኔትን ሃይል ኑሯቸውንና ማህበረሰባቸውን ለማሻሻል ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡፡ የተጠቃሚዎችን መረጃዎችን ደህንነታቸው አስተማማኝ በሆነ ከባቢዎች የማግኘት መብታቸውን ቤተ-መጻህፍት ይጠብቃሉ፡፡ ቤተ-መጻህፍት በማህበራዊ ኑሮና በባህል እንቅስቃሴ ውስጥ ሁሉንም ያሳትፋሉ፡፡ እንዲሁም ሰዎች አገልግሎት በሚሰጧቸው ህዝባዊ ተቋማት ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚረዱ ከመሆኑም በላይ ለህብረተሰባዊ ተሳትፎና ዜጎች የመንግሥት አገልግሎቶችን በቀላሉ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ አማካይነት ለማግኘት እንዲችሉ ለመርዳት ዝግጁ ሆነው የሚገኙ ሥፍራዎች ናቸው፡፡

## ቤተ-መጻህፍት የመላው ዓለም እውቀት መገኛ ሥፍራዎች ናቸው

ቤተ-መጻህፍት ትምህርት፣ የሥራ ዕድል እና ማህበረሰባዊ ዕድገት ለማስገኘት ሚና ካላቸው ወሳኝ መሠረተ-ልማቶች ውስጥ እንደ አንድ የሚቆጠሩ እጅግ አስፈላጊ አካል ናቸው። ቤተ-መጻህፍት ትርጉም ባለውና አመቺ በሆነ መንገድ መረጃዎችን በሁሉም መልክ ማለትም በድርሳነ-መዛግብት፣ በህትመት፣ በኦዲዮ ቪዥዋል እና በዲጂታል ቅርጽ ያቀርባሉ። እንዲሁም መደበኛ፣ መደበኛ ያልሆነ እና በህይወት ዘመን የማይቋረጥ ትምህርት እንዲጠበቅ፣ እና ማህበረሰባዊ ሥነ-ቃሎች፣ ባህላዊና ሀገራዊ ዕውቀት፣ ባህላዊና ሳይንሳዊ ብሄራዊ ቅርስ እንዲጠበቅ ይደግፋሉ። ቴሌኮሙኒኬሽንን ለማሻሻልና ፈጣን የብሮድባንድ ትስስሮችን ለማቅረብ ብሄራዊ የመረጃ ፖሊሲዎች በሚቀረጹበት ወቅት ቤተ-መጻህፍት ህብረተሰቡ የመረጃና ኮሙኒኬሽን አቅርቦትና እርስ በርሱ የተሳሰረ መረጃ እንዲያገኝ በማድረግ የዕቅዱ የማይታለፍ አጋር ይሆናሉ።

## ቤተ-መጻህፍት ሙያዊ የአመራር ድጋፍ ያቀርባሉ

በቤተ-መጻህፍት ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች በቂ ሥልጠና የወሰዱና የሚታመኑ ሁሉም ሰዎች የሚፈልጓቸውን መረጃዎች ለማግኘት እንዲችሉ ለመርዳት በጽናት የቆሙ ናቸው። የቤተ-መጻህፍት ሠራተኞች ሰዎች የመረጃ ዓለምን በቅጡ ለመረዳትና በዚህ የመረጃ ዓለም ውስጥ በብቃት ለመሳተፍ እንዲችሉ የሚረዳቸውን የመረጃ ዕውቀት እንዲያገኙ ሥልጠናና ድጋፍ ይሰጣሉ። የቤተ-መጻህፍት ሠራተኞች ባህላዊ ቅርሶችን ጠብቆ በመያዝና ለተጠቃሚዎች በማቅረብ እንዲሁም ሰዎች ማንነታቸውን እንዲያበለጽጉ በመደገፍ ረገድ የባህል ቀዳሚ መሪዎች ናቸው።

## ቤተ-መጻህፍት በርካታ ባለድርሻዎች ያሉበት ህብረተሰብ አንድ አካል ናቸው

ቤተ-መጻህፍት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በተለያዩ ሁኔታዎች በውጤታማነት ይሰራሉ። ከአካባቢያዊና ብሔራዊ መንግሥታት፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ የፋይናንስ ድጋፍ ከሚያቀርቡ ድርጅቶች፣ እና ከግል እና ኮርፖሬት ድርጅቶች ጎን በመሆን ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ያቀርባሉ። የቤተ-መጻህፍት ሠራተኞች ከመንግሥታት፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ከንግድ ድርጅቶች፣ ከምሁራን እና ከቴክኒክ ባለሙያዎች ጎን በመቆም የፖሊሲ ግቦችን በማዘጋጀት የሚሳተፉ ንቁ ተዋናዮች ናቸው።

## የፖሊሲ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ ለቤተ-መጻህፍት እውቅና ሊሰጣቸው ይገባል

ዘላቂነት ያለውን ልማት ለማስገኘት የሚረዱ መረጃዎችን በማቅረብና እንደመረብ የተሳሰረ የመረጃ አገልግሎት በማቅረብ ረገድ ቤተ-መጻህፍት ወሳኝ ሚና ያላቸው እንደመሆኑ መጠን ፖሊሲ አውጪ አካላት የቤተ-መጻህፍት አገልግሎት አቅርቦት እንዲጠናከር ማበረታታትና የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎችና ሌሎች የመረጃ ሠራተኞች ያላቸውን እውቀት በማህበረሰብ ደረጃ የሚገኙ የልማት ችግሮችን በመቅረፍ እንዲረዱ ሊጠቀሙባቸው ይገባል።

በዚህም ምክንያት ፖሊሲ አውጭዎችና_የልማት ሠራተኞች እነዚህን እጅግ ጠንካራ ነባራዊ የልማት ሃይሎች በአግባቡ እንዲጠቀሙባቸውና እንዲሁም ከ **2015** ዓመተ ምህረት በኋላ የሚቀረጹ የልማት ማዕቀፎች፡-

- መረጃዎችን ካለአንዳች እክል በቀላሉ የማግኘት ጉዳይ ልማትን በመሠረታዊነት በመደገፍ ረገድ ያለውን ሚና እንዲያውቁ፤

- ቤተ-መጻህፍትና የቤተ-መጻህፍት ባለሙያዎች የልማት ጥረት አካል መሆናቸውን እንዲቀበሉ፤

- *መረጃን፣ የመረጃ ትስስርንና የሰው ሃይልን በማቅረብ ልማትን የሚደግፉትን እንደ ቤተ-መጻህፍትና ሌሎች መሰል ህዝባዊ አገልግሎት የሚያቀርቡ አካላት ያሉ የመረጃ ማዕቀፎችን እንዲደግፉ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ሃገራትን እንዲያበረታቱ*

የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን_አበክሮ ይጠይቃል፡፡

እ.ኤ.አ. በኦገስት 16, 2013 በቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ተቋማት ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን ከፍተኛ አመራር አካል በሲንጋፖር የፀደቀ፡፡